# አማራው ሲደመር የማንነት ጥያቄን ይፋ በማድረግ ይሁን

አብነት ሁነኛው

ዶ/ር አብይ ያሳዩትን አስተዳደራዊ አርቆ አስታዋይነት ተከትሎ በሸዋ ባሉ የአማራ ከተሞች፤ በጎንደር፤ በባህርዳር፤በኮምቦልቻ፤ወልዲያ፤ደጀን፤ዳንግላ፤ገንዳውሀ፤ሰቆጣ፤ስንቱ ተዘርዝሮ ያልቃል ብቻ በመላው አማራ ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ ከድጋፉ ጎን ያለምንም ማወላወል ከዳር እስከዳር በአንድ ድምፅ የአማራን ብሔረተኛነት ለወዳጁም ሆነ ለጠላቱ ባደባባይ እንዲያውቁለት ማድረግ ችሎዋል። አንግቦ በወጣቸው መልዕክቶቹ የአማራ መፈናቀል ይቁም፤ወልቃይትና አካባቢው እንዲሁም ከወሎና ጎጃም የተወሰዱት አንጡራ መሬቶቻችን ይመለሱ፤ ብአዴን ራሱን አማራውን ከማይወክሉ ጅቦች ያጥራ፤ከሱዳን በኩል ቀጥሎ የሚገኘው ወረራ ይቁምና ድንበራችን ይመለስ፤አንድ አማራ ለሁሉም አማራ ሁሉም አማራ ለአንድ አማራ፤ ወዘተ. የሚሉትን የተጋድሎውን አቅሞች ለብአዴንና የዶ/ር አብይ ኢሕአዴግ በተለይም ለወያኔው ሕወሐት መሬት የረገጠ ቁርጠኛ ውሳኔ እወቁት ብሎ ለአንዴና መጨረሻ ፊታቸው አቅርቦላቸዋል። አማራው አምስት አመት ባልሞላ እጅግ አጭር ግዜ ውስጥ እዚህ ይደርሳል ብለው ባይገምቱም 'የተናቀ ያስረግዛል' ነውና እነዚህ አምባገነኖች ሳይወዱ በግድ ሀቁን መዋጥ ካልቻሉ ውሎ አድሮ ምን ሊከሰት እንደሚችል ግን ሳይገባቸው የሚቀር አይመስለኝም። አማራ በሙሉ የሐምሌ 5 ቀን የተደወለውን የአማራ ብሔረተኝነትና ማንነት ተጋድሎ ማብሰሪያ ለዘለዓለም እናከብረው እያልኩ የሚከተሉትን ነጥቦች እንድትመለከቱ ጥሪ አቀርባለሁ።

1/ባለው መንግስት ፖሊሲ ለ 27 ዓመት መጤ ተብሎ ሲፈናቀል፤ንብረቱን ሲቀማና ሲገደል ለኖረው የአማራ ሕዝብ የዶ/ር አብይ አስተዳደር በይፋ አማራውን ይቅርታ ጠይቆ የደምና በደል ካሳ ይክፈል።

2/በመላው አገሪቱ መፈናቀል ሕገወጥ መሆኑን አስመልክቶ ወንጀለኞችን በሕግ ፊት አቅርቦ የሚያስቀጣ አዋጅ በሸንጎው ይደንገግ።

3/ከመላው ኢትዮጵያ የተፈናቀሉት አማራዎች ወደ ነበሩበት በክብር ይመለሱ።

4/አማራ በመሆናቸው ብቻ እንዳይደራጁና በምርጫ እንዳይወዳደሩ በተከለከሉባቸው ክልሎች ሙሉ የሆነ መብታቸው ይረጋገጥላቸው።

5/በቅንቅቸው እንዲማሩ፤እንዲዳኙና አስተዳደራዊ ጉዳዮች እንዲፈጸሙላቸው ይሁን።

6/በአማራ ክልል ማንኛውም ሰው በክልሉ 2 ዓመት ከኖረ የመምረጥ፤የመመረጥ ወዘተ. መብቶች የሚሰጠው አሰራር በሌሎች ክልሎች የአማራው መብት እስኪረጋገጥ ድረስ ብአዴን በሕጉ አንቀጽ ላይ እገዳ ያድርግ።

7/በመተከልና ቀማሺ የአማራ ልዩ ዞን ይመስረት። እዚህ ላይ መተከል አማራ መሆኑን አልዘነጋሁትም። ሁመራ፤ ወልቃይት፤ጠገዴ፤ጠለምት፤ራያ ቅንጣት ያህል ሳይሸራረፍ በጉልበት ወያኔ ትግሬዎች የቀሙን ስለሆነ እንዳሉ ወደ እናትና አባት አማራ አገራቸው ይመለሱ። በዚህ አቅም አንድም አማራ አይደራደርም።

8/በኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ፤ምዕራብ ሸዋ፤በደቡብ ሸዋ፤በምስራቅ ሸዋ አማራው ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድርና በቅንቅው እንዲጠቀም ይሁን።

9/ልክ በድሬዳዋ ኦሮሚያና ኢትዮ ሶማሌ ያገኙትን አስተዳደራዊ የጥቅም መጋራት በአዲስ አበባ (በረራ) ላይ አማራው ከኦሮሞው ጋር በዕኩልነት ተጠቃሚ ይሁን። የአማራው ጉልት የሆነችው የአፄ ዳዊት በረራ ከተማን ለኦሮሞው ብቻ አስተላልፎ የሚሰጥን ማንኛውም ውሳኔ የአማራ ሕዝብ በሙሉ የማይቀበለው እንደሆነ በግልጽ በአማራ ማንነት ተጋድሎ ይቀንቀን። ይህን ያልኩበት ዋናው ምክንያት ከተማዋ መላው ኢትዮጵያዊ የሚኖርባት ስለሆነችና የአፍሪቃም ዕንብርትነትዋን ተገንዝቤ ነው። ታሪካዊ ማስረጃዎችን ብቻ እንመልከት ካልን ግን ውሳኔው አዲስ አበባ (በረራ) የአማራ ነች የሚለው ይሆናል።

10/አማራውን አግልሎ የተጻፈው ሕገመንግስትና የክልል አስተዳደር አማራውን ባሳተፈ መንገድ እንዲስተካከ መደረግ ይኖርበታል።

11/የሕወሐት/ኢሕአዴግ መንግስት በሚስጥር ውለታ ፈጽሞ ለሱዳን አስተላልፎ የሰጠውን የአማራ ጎንደር መሬት ጉዳይ ለሕዝብ በይፋ ማሳወቅ አለበት። አማራው ባልተሳተፈበት በማንኛውም ወገን ድንበርን አሳልፎ የመስጠት ወሳኔ አዲሱ የአማራ ትውልድ አይቀበለውም። በተደጋጋሚ በሱዳን ወታደሮች አማራው ሕዝብ ላይ የሚፈፀሙ ውንብድና 'መከላከያ ሀይል' የሚባለውና የክልሉ ታጣቂ ቡድን ለምን አማራውን እንደማይታደጉና የአገር ድንበርን እንደሚያስደፍሩ የዶ/ር አብይ አስተዳደርና ብአዴን በይፋ ማብራሪያ መስጠት ይኖርባቸዋል።

12/በአማራ ክልል ሲቪል ሰርቪስ የአማራው ወጣት ተጠቃሚ እንዳይሆን በሕወሐት ትግሬዎች ከታች እስከ ላይ የሚደረገው ብዝበዛና ሕገወጥ አሰራርን ብአዴን እንዲለውጥ፤እስካሁንም ይህ እኩይ አሰራር ለምን ቀጥሎ እንዳለ ለመላው አማራ ባደባባይ ምክንያቱን እንዲያቀርብ መደረግ አለበት።

13/በአማራ ፖሊስ፤ሚሊሻና ልዩ ሀይል ውስጥ ተሰግስገው አማራውን እያሰቃዩ ያሉ ሕወሐቶች ሙሉ በሙሉ ከስልጣናቸው ተነስተው በአማራ ልጆች ይተኩ።

14/የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም (አብቁተ) ለአማራው ሕዝብ አገልጋይ እንዲሆን አመራሩ በሙሉ ይለወጥ።

15/የአማራ ልማት ማህበር (አልማ) ትኩረቱ ለአማራ ሳይሆን ለትግራይ ስለሆነ እንደገና የአማራውን ጥቅም መሰረት አድርጎ እንደ አዲስ ይዋቀር።

16/የጥረት ኮርፖሬትን አማራዊ ገፅታና አላማ ላይ ብቻ ያነጣጠሩ የመዋለ ነዋይ (ኢንቨስትመንት) ስራ እንዲሰራ ካስፈለገ ሀላፊን መለወጥ በቂ ስላልሆነ ከአማራ ሽማግሌዎች፤ባለሀብቶች፤የሀይማኖት አባቶች፤ወጣቶች፤ገበሬዎች፤ እንዲሁም ምሁሮች (ልሂቃን) የተውጣጣ ኮሚቴ ተሰይሞ መመሪያ፤ደንብና ዓላማ ወዘተ. ጥረት ባለ መልኩ አሁን ያለውን አሰራርና አቅጣጫ በሚያቀርቡት ሪፖርት ላይ ተመስርቶ እንዲለወጥ መደረግ አለበት።

17/በአማራ ክልል ብቻ በልዩና በተጠናከረ ሁኔታ የሚተገበረውን የቤተሰብ ምጣኔ ፖሊሲ አማራው ራሱን በአዲስ ትውልድ እንዳይተካ ደንቃራ ስለሆነበትና ከዘር ማጥራት ወንጀል ጋር የተቆራኘ በመሆኑ የአማራ ሴቶች በራሳቸው ፍላጎት ላይ ብቻ በተመሰረተ የቤተሰብ ምጣኔን ተግባራዊ ማድረግ እንዲያስችላቸው በአያሌው ጎበዜ ዘመን በወያኔ ተፅዕኖ የወጣውን አስገዳጅ ደንብ እንዲሰረዝ ማድረግ።

18/አማርኛ ቋንቋ እንዲዳከም በክልሉ 93% የሚሆነው ሕዝብ የአፍ መፍቻው መሆኑ እየታወቀ በክልሉ 12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና እንዳይካተት የተደረገው አካሄድ አሉታዊ ተፅዕኖ በዕድገቱ ላይ ስላሳደረበት ተመልሶ በፈተናው ላይ እንዲካተት ይሁን። አሁን እንዲጎለብቱ የተደረጉትን የአዊና ሕምጽኛ ቋንቋዎች ግዕዝን ጨምሮ መላው የአማራ ተማሪዎች ቢያንስ ከ 4ኛ እስከ 10ኛ ክፍል እንዲማሩ ቢደረግ የክልሉን ሕዝብ ከባህልና ታሪክ

የጋራነት በመቀጠል ጥብቅና ልዩ አንድነት ስለሚፈጥርና በአማራው መካከል እርስ በርሱ ባይተዋር እንዳይሆንና በቅንቅዎቹ ተነጋግሮ እንዲግባባ ስለሚያስችለው የክልሉ ት/ት ፖሊሲ በዚህ ረገድ በተግባር ይስተካከል።

19/የተፈናቀሉ አማራዎችን ለመደገፍ፤ጣናን ከእምቦጭ አረም ለመከላከል፤በወያኔ ጥይት በግፍ የተገደሉትን የአማራ ልጆች ቤተሰቦች ለማገዝ ወዘተ. በግልና በቡድን ሆኖ አለኝታ ለመሆን የተጀመሩትን አማራዊ ትብብር ጠንካራ መሰረት ኖሮት ባስፈላጊው ግዜ ቅሚ ደራሽ እንዲሆን አማራ አቀፍ ዕድር በውጭም በአገር ውስጥም እንዲቋቋም ማድረግ።

20/የአማራ ብሔረተኝነትና ተጋድሎ በምንም ዓይነት ሁኔታ መቀዛቀዝ ስለሌለበት ሁሉም አማራ ተደራጅቶም ይሁን በተናጠል በጉልበቱ፤በገንዘቡና እውቀቱ የቻለውን (በአቅሙ) አስተዋፆ ያድርግ።

በመጨረሻም "ዛሬ በተለያዩ ቦታዎች ያሉ ተቃዋሚዎች መጥተው በጋራ እንዲሰሩ ጥሪ እየተደረገላቸው ነው። ነገር ግን ለኔም ውስጤን ያመመኝ ነገር አለ። ምንም እንክዋን ኢትዮጵያዊነት ጥሩ በመሆን ቢሆንም፤ መዳመር በጋራ መኖር ታላቅነት ቢሆንም አመጣጡ በምን መልኩ ነው? የሽግግር መንግስት ልናቋቁም ነው? ወይንስ በነበረው ወይም ደግሞ በተቀደደልን ቦይ ልንፈስ ነው? " በሚለው የብርቅዬ እናታችንና እህታችን ወይዘሮ እማዋይሽ አለሙ ታሪካዊ አነጋገር ጥቅስ አስተያየቴን አቅርቤያለሁ።
አብነት ሁነኛው ነኝ!